**የኢትዮጵያውያን ማህበር በኖርዌ (ኢማኖ) መግለጫ**

ኢትዮጵያ በተከታታይ በደረሰባት የፖለቲካ፣ የማህበራዊ ቀውስና ድህነት ሳብያ ልጆቿ ለስደት ተዳርገዋል። ኢትዮጵያ በስደቱ ምክንያት የሰራተኛውን ሃይል፣ የተማሩ፣ የተመራመሩና ረዳት የሚሆኗትን ልጆቿን አጥታለች። ስደት - ከጦርነቱ፣ ከድህነቱ፣ ከረሃቡና ከርዛቱ፣ ከበሽታው ጎን የሚደመር የሃገራችን ዋነኛ መቅሰፍት መሆኑ ከተከሰተ እነሆ ከሶስት አስር አመታትን በላይ አስቆጥሯል። ይህንኑ አስመልክቶ ብዙ የተጻፈና የተነገረ በመሆኑ እዚህ ላይ ማንሳቱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል።

የስደትን አስከፊ ገጽታ ለማደብዘዝ አስቸጋሪ ቢሆንም ቅሉ፣ በስደት በውጪ ሃገሮች የምንገኝ ኢትዮጵያውያኖች በአንድነት ጥላ ሥር መሰባሰባችን ግን መሆን ከሚገባው ዋነኛ መፍትሄ የመጀመርያው ነው። ከሃገራችን ኢትዮጵያ ውጪ የምንገኝ እኛ ኢትዮጵያውያን የዛች ውድ እናት ሃገራችንን አምሳያ መተካት የምንችለው በጥቂቶች ትግልና ታታሪነት በተመሰረተው የኢትዮጵያውያን ማህበር (Ethiopian Community) ሥር መደራጀት ስንችል ብቻ ነው። ሆኖም ግን በዚህ አይነቱ ማህበር መደራጀት ካልፈለግን ወይንም ካቃተን ውድ ሃገራችንን በስጋም በመንፈስም የተለየናት ዓመታትን ያህል ከንቱነትንና ፍሬ ቢስነትን (futile) በጀርባችን ላይ ተሸክመን ዘልዛላውን እድሜአችንን እንገፋለን።

እትዮጵያውያኖች በተናጠል በተቋቋሙት የፖለቲካ፣ የእድር፣ የእቁብ፣ የሰፈር ልጅነት፣ የጓደኝነት፣ ወዘተ ስብስቦች መደራጀታችን ባይከፋም ቅሉ ሙሉውን ኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ሊያላብሱን ግን አይችሉም። እነዚህ ድርጅቶች ምናልባት ካንድ ከታለመ ግብ ሊያደርሱን የሚችሉ ስብስቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን ከፍ ወዳለው ሃገርን የመታደግ የእድገት ደረጃ ልንሸጋገር የምንችለው ሁላችንንም በአንድነት ባሰባሰበው የኢትዮጵያውያን ማህበራት (Ethiopian Communities) ሥር ስንደራጅ ብቻ ነው። ከፍ ያሉት የእድገት እሴቶችና መርሆች (higher values and principles) የሚፈልቁት ኢትዮጵያዊነትን ከተላበሱ የሃገር ልጆች መሃከል ነው። መልካም ስነምግባር (ethics) እንዲሁም ላቅ ያለ ግብረገባዊነት (moral) የሚጎለብቱት የኢትዮጵያዊነትን ሸማ ስንደርብ ነው። ግለኝነትና ራስወዳድነት (egoism) የሚወገዱት ኢትዮጵያንና የረጅም ዘመናት የነጻነት አርማችንን ስንመለከት ብቻ ነው። ለዚህም ነው ታድያ ባንዳንድ አካባቢዎች የተቋቋሙ ልዩ ልዩ ስብስቦች አንድን አባል ከመልመላቸው በፊት የኢትዮጵያውያን ማህበር አባልና ንቁ ተሳታፊ መሆኑን የሚያረጋግጡት። ይህ አይነቱ የአሠራር ዘዴ ለግል ጥቅም ሲሉ አቋራጭ የሚጠቀሙትን ራስ ወዳዶችን ያግታል። የክፋትና የጥፋት ሃይሎችን ቅስም ይሰብራል። ፀረ-ኢትዮጵያውያን - ሃገራዊ ጉዳዮችና ቤተሰባዊ ገመናዎች ውስጥ ዘው ብለው እንዳይገቡ በሩን ይዘጋባቸዋል፣ የውስጥ መርህንም ከማጠናከር አልፎ ኢትዮጵያዊው ማን እንደሆነ ከምግባሩ ቅንነትና ከተግባሩ ፅናት ይለያል።

ጠቅለል ባለ አነጋገር ስንደመድመው፥ እኛ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ከልብ ከተባበርን - ማህበራችንን - ኢትዮጵያ በመቃተት ስቃይዋ እንዳትቀጥል የሚረዳ የጥናትና የምርምር የታሪክና ሙዚዩም ወዘተ እንዲሁም እውነተኛ ምግባርና መስዋዕትነት የሚገለፁበት ተቋም ማድረግ አይሳነንም።

እነሆ በኢትዮጵያውያን ማህበር ሥር መሰባሰብ ልዩነቶችን የማቻቻል (harmony) ትምህርት እንድንቀስም ይረዳናል። አንድነትና ልዩነት (unity and contradiction) የእድገት ፈር ቀዳጆች መሆናቸውን እንገነዘባለን። ግባችን አንድነታችንና እትዮጵያዊነታችን በመሆኑ ለዛች በድህነት ለምትንፏቀቀው እናት ሃገራችን መፍትሄ የምንሆንበትን መንገድ በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሥር በማገልገል ንድፈ ሃሳብ (theory) ቅመራ ድረስ በኢትዮጵያውያን ማህበር ውስጥ እንማራለን። በልዩነት አንድ መሆንን (unity in diversity)፣ መልካም ፍሬ የሆነውን ትእግስትን፣ ማስተዋልን፣ ፍቅርንና መረዳዳትንም እናጎለብታለን። ለወገን ቀድሞ ደራሽነታችንንም እናስመሰክራለን። ግብዝነትንም (hypocracy) አስወግደን የጎሊና ደስታ እንጎናጸፋለን።

ወገኖች ሆይ! የነፕላቶ፣ አሪስቶትልና ሶቅራጥስ ጥበብን የማፍቀር (philosophy) ማእከል በሆነችው አውሮፓ ተቀምጠን ስለ እድገትና አንድነት ካልተማማርን ከቶ የት ብንደርስ ልንለወጥ እንችል ይሆን? የነጆን ሎክ፣ የነ ቶማስ ሆብስንና ስቱርት ሚል ጤናማና ምርታማ ፅንሰ ሃሳቦችን (healthy & productive concepts) እንዲሁም ለእድገት ቁልፍ የሆኑትን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ እሴቶችን (socio-economic values) ካልጨበጥን መጨረሻችን ምን ሊሆን ነው? አብረናቸው ከምንኖረው አውሮፓውያን ቀጠሮና ሥራን የማክበርን፣ በስብሰባ የመሳተፍን፣ ታዛዥነትን (obedience) የልማትና የአዲስ ነገር ግኝት (development and innovation) አስተሳሰብን ካላሳደግን፣ እንዳለፉት አባቶቻችን ህዝብንና ሃገርን የማስቀደምን (patriotism) እንዲሁም ለፍትህ (justice) መቆምን ካልተለማመድን ከደመ-ነፍስነት ባህርይ (instinctive behaviour) በምን እንለያለን? ለተራቡትና ለታረዙት ወገኖቻችን መድረስ ካቃተንስ እምነቶቻችንና መርሆቻችን ምን እርባና አላቸው?

ወገኖች ሆይ! ኢትዮጵያን - ኢትዮጵያ ያሰኟት የእምነት አባቶች፣ ቆራጥ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ መሪዎች፣ ፈላስፎችና አዋቂዎች፣ የጦር አርበኞች፣ ምሁራን፣ ደራስያን፣ ጋዜጠኞች፣ ስፖርተኞች፣ የሥነ ጥበብና የኪነት ፈርጦቻችን ድርሻቸውን ተወጥተው ከኢትዮጵያችን በሞት ተለይተዋል። አንዳንዶቹም ሲለፉና ሲታገሉ ቆይተው በለጋነት እድሜአቸው ተቀጭተዋል። እንግዲህ በህይወት ካለነው የአባቶችንና እናቶችን አደራና ሃላፊነት ከተሸከምነው ኢትዮጵያውያን መሃከል እኛ በስደት እንገኛለን። ታድያ ቀኑ ሳይጨልምብን ድርሻችንን ብንወጣ ሌላው ቢቀር እንኳን ለልጆቻችን ማፈርያ ከመሆን እንድናለን። የታደሉት ወገኖቻችን የኢትዮጵያዊነትን ዓርማና ፅናትን ለቀሪው ትውልድ

አውርሰው በህዝብ ፍቅር ታጅበው በሰላም ሲያርፉ፣ እኛ ስደቱ ተመችቶን ስንኩራራ ነገ ልጆቻችን ይጠይቁናል፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ያዝንብናል።

የኢትዮጵያዊነት የባለአደራነት ሃላፊነትና ግዴታችንን እንወጣ ዘንድ የሁሉም ነገር ባለቤት የሆነው እግዚአብሄር ይርዳን።

የኢትዮጵያውያን ማህበር በኖርዌ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ
ኦስሎ - ጁን - 2009